# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 250 የካቲት 21 2005 ገጽ 1


**የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ፡- ምርጫችን ሁለት ነው። ወይ "ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል እያልን የቁም ሞት ኑሮአችንን መኖር" አሊያም ወያኔን አስገድደንም ሆነ አስወግደን የሚገባንን የኩሩ ህዝብና ሀገር ስብእናችንን ማስመለስ እና ሀገርን ከማዳን ከሞራላዊ ግዴታ ተጠያቂነት ነጻ የመሆን።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን የአዲስ አበባ ከተማን በጩሀት ሲያናጉ ዋሉ

ላለፈው አንድ አመት ድምጻችን ይከበር፣ መብታችን ይጠበቅ በማለት እጅግ ጥንካሬና ጽናት ባለው መንፈስ የዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ ወጥረው የሚገኙት ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በትናንትናው እለትም የተቃውሞ ድምጻቸውን ሲያሰሙ የዋሉ ሲሆን፣ በትናንቱ ተቃውሞአቸው የአዲስ አበባ ከተማን በድምጽ ሲያናውጡ መዋላቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

ሙስሊሙ አንድ ነው፣ አንለያይም፣ ለእምነታችን እንሞታለንና የመሳሰሉትን መፈክሮች በከፍተኛ ቁጣ ሲያሰሙ የዋሉት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን፣ ዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ መሪዎቻቸውን ከማሰርና በተናጠልም እጅግ በርካታ ሙስሊሞችን የማዋከብና የድብደባ ተግባር ቢፈጽምባቸውም፣ እንደ ቀድሞው ሁሉ በትናንትናው እለትም ፍጹም ለአላማቸው ቁርጠኛ መሆናቸውንና ከሌሎች ወንድሞቻቸው ጎን የሚቆሙ መሆናቸውን ሲያሳዩና ሲያረጋግጡ ውለዋል።

አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ላለፈው አንድ አመት በጽናት ለመብታቸው በመቆም እየታገሉ ያሉ ሙስሊሞችን ተቃውሞ ለማስቆም የተለያዩ ሙከራዎችንና በደሎችን ማስፈራሪያዎችን ቢያደርስም የሙስሊሞቹ ተቃውሞው ከእለት እለት እየጨመረና እየተስፋፋ ከመሄድ በስተቀር መቀነስ አለመቻሉ በአምባገነኖቹ ስፈርና ለፍርፋሪ ባደሩ ቡችላዎች ላይ እጅግ ከፍተኛ ድንጋጤ ፈጥሮ መቆየቱን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

ቀደም ብሎ በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ባለፈው ፌብሩዋሪ 23 በዋይት ሀውስ ፊት ለፊት ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸውና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ላይ እየፈጸመ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ማውገዛቸውና የሙብት ትግል አጋርነታቸውን መግለጻቸው ይታወሳል።

አፋኙ የወያኔ አገዛዝ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እጅግ አስከፊና የግለሰቦችን ንብረት መዝረፍን የጨመረ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እየፈጸመ ያለ መሆኑ፣ የዘረኛው ወያኔ ፖሊሶች እጅግ በርካታ ሙስሊሞችን አፍነው መውሰዳቸውና እነኝሁ ግለሰቦች እስካሁን ያሉበት ስፍራ አለመታወቁም ቀደም ብሎ መዘገቡ ይታወሳል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እነኚህን ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ለመብት ከሚያደርጉት ትግል ለማስቆም እንዲህ አይነት የከፉ ርምጃዎችን ቢወስድም ሙስሊሞቹ አሁንም በጽናት እየታገሉ መሆናቸውንና ይህን አቋአማችውቸውንም አጠናክረው እንደሚቀጥሉ የገለጹለት መሆኑን ዘጋቢያችን አስታውቁአል።

## በአዲስ አበባ የቤት አፍርስ ዘመቻ ተጀመረ፣ የዘመቻው ጠቅላይ አዛዥ ኩማ ደመቅሳ መሆኑ ታወቀ

በግንባታና በኢንቨስትመንት ሽፋን ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ነዋሪዎች እየተፈናቀሉና ከቀያቸውም እየተባረሩ እንደሆነ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ሪፖርት ገለጸ። ከዘጋቢያችን የደረሰን ሪፖርት እንደሚያሳየው በኢንቨስትመንትና አንዲሁም በመኪና መንገድና በባቡር ሀዲድ ግንባታ ስም በቦሌ፣ በቂርቆስ፣ በልደታ፣ በኮልፌ ቀራኒዮና በንፋስ ስልክ ክፍለከተሞች ካለፉት ሁለት ሳምንት ወዲህ ዜጎችን ከሕግና ስርዓት ውጪ የማፈናቀሉን ሥራ ተፋፍሞ ቀጥሉአል።

ቀደም ብሎ ባላፈዉ ሐምሌና ነኃሴ ወራት አላግባብ ቤት ሰርታችኋል የሚል ሰንካላ ምክንያት ከ30 ሺ በላይ የሚሆኑ የላፍቶ ክፍለ ከተማ አባዎራዎች ቤት መፍረሱ በዚህም ምክንያት ሴቶችና ህጻናት ባዶ ሜዳ ላይ መበተናቸው ይታወሳል። ቀደም ብሎ በነኝሁ ኢትዮፕያዊያን ላይ ግፍ እንዲፈጸም ያደረገው ኩማ ደመቅሳ ያ ሁሉ ክፋትና ጭካኔ አልበቃ ብሎት አሁንም በልማት ስም የአዲስአበባን ነዋሪ የማፈናቀል ስራውን በዘመቻ መልክ ማከናወኑ በደል እየተፈጸመባቸው የሚገኙትን ዜጎች እጅግ እያስቆጣ መሆኑን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጹአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ወያኔ አብያተ ክርስትያናትን ወደ ገንዘብ መሰብሰቢያ ተቋምነት እየተቀየረ መሆኑ ታወቀ

የወያኔ አገዛዝ በአንድ በኩል መንግስት በሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ካድሬዎቹን ሐይማኖታዊ ካባ እያለበሰ በየቤተክህነቱ በመስግሰግ የማምለኪያ በታዎችን ወደ ገንዘብ መሰብሰቢያ ተቋምነት እየቀየራቸዉ መሆኑን ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ምንጮቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን የአማራ ስርአት ደጋፊ ናት የሚል ጽንፈኛ አቋም ገና በረሃ ዉስጥ እያሉ የወሰዱት የወያኔ ዘረኞች ቤተክርስቲያኒቱን ማመስ ከጀመሩ ሰላሳ አመት ያለፋቸዉ ሲሆን አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በሁዋላ ደግሞ የበረሃዉን እኩይ አላማ ማስፈጸም እንዲቻላቸዉ ህጋዊዉን ፓትሪያሪክ ብጹዕ አቡነ መርቆሬዎስን ከመንበራቸዉ አስነስተዉ የአምላካቸዉን ሳይሆን የነሱን ትዕዛዝ የሚሰሙትን አባ ጳዉሎስን መሾማቸዉ የሚታወስ ነዉ።

አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ለቤተክርስቲያኒቱ ቅርበት ያላቸዉ ብዙ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት መልዕክት እንደገለጹት ዛሬ አዲስ አበባ ዉስጥ ምዕመናን በብዛት የሚሄዱባቸዉ እንደ መንበረ ፓትሪያሪክ ቅድስት ማሪያም፤ ቦሌ መድሃኔአለም፤ የካ ሚካኤልና መርካቶ ቅዱስ ራጉኤልን የመሳሰሉ አብያተ ክርስትያናት የሚመሩት የአምነት አባት የሆኑ አባቶች ሳይሆኑ ወያኔ ምዕመኑን እንዲከፋፍሉና ገንዝብ እንዲሰበስቡ ያቀመጣቸዉ የቄስ ልብስ የለበሱ ካድሬዎች ናቸዉ። አንዳንዶቹ ካድሬዎች በተለይ ለወያኔ መሪዎች ቅርበት ያላቸዉ ካድሬዎች ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተክርስቲያን እንደሚመላለሱ ለማወቅ ተችሏል። ለምሳሌ አባ ተጠምቀ መድህን ገብረኢየሱስ የተባሉ አባት በአጭር ግዜ ዉስጥ በስድስት አብያተክርስቲያናት ዉስጥ ወያኔን ወክለዉ ሰርተዋል።

ወያኔ አብያተክርስቲያናትን በአንደ በኩል በከፍተኛ የገንዘብ ምንጭነት የሚጠቀምባቸዉ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ፈጣሪዉን ለማምለክ ወደየአብያተክርስቲያናት የሚሄደዉን ህዝብ በትናንሽ ጉርሻ እያታለለ ለራሱ እኩይ አላማ ለማሰለፍ በየዞኑ ባሰማራቸዉ ካድሬዎቹ አማካይነት ከፍተኛ የፖለቲካ ስራ እየሰራ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። አንድ ተቀማጭነታቸዉ አዲስ አባባ ዉስጥ የሆን የምዕራቡ አለም የፖሊቲካ ተንታኝ እንደተናገሩት የወያኔ አገዛዝ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ያተኮረዉ ከሙስሊሙ ህብረተሰብ የሚደርስበትን ጫና ለመቀነስና ሙስሊሙንና ክርስቲያኑን በማጣላት እሱ ተዝናንቶ ለመኖር ካለዉ ምኞት የተነሳ ነዉ ብለዋል። በእርግጥም ዛሬ በግልጽ እንደሚታየዉ ከአንድ አመት በላይ ለዘለቀዉ የሙስሊሙ ህብረተሰብ "መብታችንይከበር" ለሚል ሰላማዊ ጥያቄ ተገቢዉን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ወያኔ ያተኮረዉ የሙስሊሙን ህብረተሰብ የመብት ጥያቄ ከሸሪያ ወይም ከስልጣን ጥያቄ ጋራ በማያያዝ ሙስሊሙንና ክርስቲያኑን ማጣላት ነዉ።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአምስት ዓመታት ጊዜያት ውስጥ ብቻ 196 ፕሬሶች ከሕትመት ውጪ መሆናቸው ተዘገበ

በኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚ ፣ በስፖርት፣ በሃይማኖት፣ በፍቅር፣ በኪነጥበብ እና በመሳሰሉት ርዕሰ ጉዳዮች አተኩረው ይታተሙ ከነበሩ 235 የፕሬስ ውጤቶች መካከል 196 ያህሉ በተለያየ ምክንያት ከህትመት ውጪ መሆናቸውን የአገዛዙ ብሮድካስት ባለስልጣን ሰሞኑን በድረገጹ በለቀቀው መረጃ አስታወቀ።

ባለስልጣኑ ከየካቲት 2001 እስከ ጥር 2005 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ለ91 ጋዜጦችና ለ144 ያህል መጽሔቶች በድምሩ ለ235 ያህል የፕሬስ ውጤቶች የምዝገባ የምስክር ወረቀት መስጠቱን አስታውሶ ከነዚህ መካከል እስከ ጥር ወር 2005 ዓ.ም ድረስ መዝለቅ የቻሉት 18 ጋዜጦች እና 21 ያህል መጽሔቶች በድምሩ 39 ያህል የፕሬስ ውጤቶች ብቻ መሆናቸውን አመልክቷል።

ባለስልጣን ተብየው በአምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በአስደንጋጭ መልኩ ፕሬሶቹ ከሕትመት ውጪ የሆኑበትን ዝርዝር ምክንያት ማስረዳት ካለመቻሉም በላይ በያዝነው የካቲት ወር 2005 ዓ.ም "መሰናዘሪያ" እና "አዲስታይምስ" የተባሉ ጋዜጣና መጽሔት ከሕትመት ውጪ በመሆናቸው በሕትመት ላይ ያሉት ፕሬሶች ጠቅላላ ቁጥር ወደ 37 ዝቅ እንዲል ሆኗል።

ዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን ሃሳባቸውን በነጻነት እንዳይገልጹ ሌት ከቀን እንደሚሰራ የሚታወቅ ሲሆን በርካታ የህትመት አዘጋጆችና ባለቤቶች ከፍተኛ የሆነ እንግልት እስርና ድብደባ ሲፈጸምባቸው እንደቆየ በስፋት መዘገቡ ይታወሳል።

## የሳጅን ዘመድኩን ዛቻ እና ትርጉሙ

ባለፉት ሳምንታት በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ክፈለ ከተማዎች የወያኔ መንግስት ፓሊሶችና ደህንነቶች በሙስሊሙ ወገኖቻችን መኖሪያ ቤቶች በመዘዋወር ዝርፊያ የተቀላቀለበት አሸባሪ ብርበራና ፍተሻ ሲያካሄዱ ሰንብተዋል። ይህ ብርበራ በአይነቱ ፍጹም ከሆን የወሮባላ ተግባር የተለየ እንዳልሆነ የደረሰባቸው፣ ያዩና የሰሙ ሁሉ የሚመሰክሩት ነው።

የፍርድ ቤት ትእዛዝ ለይስሙላ እንኳን ያልያዙ ጭንብል ያጠለቁ ፓሊሶችና ደህነነቶች ጨለማን ተገን በማድረግ በር እየበረገዱ በመግባት ቅዱሳን መጻሃፍትን፣ ሞባይልን፣ ቴሌፎኖን እና ወርቅ በግፍ መዘረፋቸውን ሰለባዎቹ አረጋግጠዋል። ይህ በእነዚህ ንጹሃን ሙስሊም ወገኖች ላይ ከተፈጸመው ድብደባ፣ ማስፈራሪያና ማስደንገጫ ተጨማሪ መሆኑ ነው።

የእነዚህን አሳዛኝ ግፈኛ ተግባር የሰማው የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ዜናውን በየካቲት 14 ቀን 2005 አ.ም ምሽት ዘግቦ ነበር። በዚህ ዘገባ ላይ የቪ.ኦ.ኤው ጋዜጠኛ የሰለባዎቹን ምስክርነትና አስተያየት ብቻ ማቅረብ ተገቢ ያልመሰለው ፕሮፌሽናሉ ጋዜጠኛ፣ ሚዛናዊ ዘገባ  ለማቅረብ ድርጊቱ ተፈጸመባቸው ወደተባሉት ክፍለ ከተማዎች የፓሊስ አዛዦች መደወል ነበረበት። ይኼኔ ነበር ጋዜጠኛው ሳጅን ዘመድኩንን ያገኘው። ይህን የመንግስት ወንጀል እንዲያስተባብሉ እድል የተሰጣቸው ሳጅን ዘመድኩን የሰጡት መልስ ሰዋዊ ሳይሆን አውሬያአዊ ነው ማለት ይቻላል።

የተሰራውን ግፍ መዘገቡ ያናደዳቸው የፖሊስ አዛዦች ጭራሹኑ ጋዜጠኛውን ራሱን አሁን መጥቼ አስርሃለሁ የሚል መልስ ነበር የሰጡት። እብሪተኛው ሳጅን ጋዜጠኛው እንኳን ዋሽንግተን መንግስተ ሰማያትም ገብቶ እንደማያመልጠው ካዛቱ በኋላ ቃለ ምልልሱ አለቀ።

ይህን ቃለ ምልልስና የሳጅን ዘመድኩን ዛቻ ስንሰማ ቅጽበታዊ ምላሻችን ሳቅና መገረም ሊሆን ይችላል። ከዚህ የደንቆሮ ሃሳብ ከሚመስል አስቂኝና አስገራሚ አነጋገር በስተጀርባ ግን በእጅጉ የሚያሳዝን፣ የሚያስለቅስና የሚያስቆጭ ትርጉም አለው። የሳጅን ዘመድኩን ጥያቄ አመላለስ የልዩ አጋጣሚ ጉዳይ (Isolated Event) አይደለም። እንደዚያ ከመሰለን ክፉኛ ተሳስተናል። በሳጅን አንደበት የሰማነው አውሬ ወይም የህወሃት ድምጽ ህዝባችን በእየለቱ ቁም ስቅሉን የሚያሳየውን የወያኔ የየእለቱን ዘረኛ ቋንቋ እና ተግባር ነው። ሳጅን ዘመድኩን የተናገረው የሰለጠነበትንና ወያኔ የወሰነውን ነው በእሱ ልሳን የሚናገረው።

ወያኔዎች የፈለገንን አድርገን አዋርደን እንገዛችኋለን፤ ምን አባታችሁ ትሆናላችሁ ነው የሚሉን በወያኔኛ ቋንቋ። ሳጅን ዘመድኩን እንደምንገምተው ደንቆሮ አይደለም። ወያኔ ውስጥ ያደገ ወያኔኛ የተማረና የሰለጠነ፣ ሁሉንም ጣቢያዎች ከሚያዙት ሰዎች አንዱ ነው። ትእዛዝ ፈጻሚ ወያኔ ነው። ህዝብ ደሞዝ የሚከፍለው የህዝብ ተቀጣሪ ነኝ ብሎ አያምንም። እንደሁሉም ወያኔዎች እየዘረፈ የሚኖር ሽፍታ ነው። ህግና ህገ-መንግስት ለጌጥ የተቀመጠ መሆኑን ወያኔዎች ሁሉ ያውቃሉ። ተናግረውታልም።

በሳጅን ዘመድኩን አራዊታዊ አነጋገር ስቀን ከሆነ የሳቅነው በራሳችንና በህዝባችን ሰቆቃ ነው። በራሳችን ውርደት ለመሳለቅ አይተናነስም።ሀገራችን በእንደ እነ ሳጅን ዘመድኩን ያሉ ሰዎች ነው የምትመራው። ትልቅ ውርደት ላይ ነን። ሀገራችን ከውረደት፣ ህዝባችንን ከሰቆቃ የማዳን ግዜው አሁን ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ፡- ምርጫችን ሁለት ነው። ወይ "ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል እያልን የቁም ሞት ኑሮአችንን መኖር" አሊያም ወያኔን አስገድደንም ሆነ አስወግደን የሚገባንን የኩሩ ህዝብና ሀገር ስብእናችንን ማስመለስ እና ሀገርን ከማዳን ከሞራላዊ ግዴታ ተጠያቂነት ነጻ የመሆን።

እንዳንሳሳት! የሳጅን ዘመድኩን አራዊታዊና እብሪታዊ ቋንቋ ወያኔያው የእለት ተእለት ዘይቤ ነው። ስለዚህ ጀንበር ቁልቁል ሳትጠልቅብን ወያኔን አስገድዶ ለመጣል ከሚንቀሳቀሰው ህዝባዊ ሃይል ጋር በመሆን የመታገያ ጊዜው አሁን ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## ወያኔ አብያተ ክርስትያናትን ወደ ገንዘብ መሰብሰቢያ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ ዉስጥ ከፍተኛ ህዝብ ከሚሰበሰብባቸዉ ቤተክርስቲያኖች ዉስጥ አስራ ሦስቱን የሚያስተዳድሩት የትገራይ ተወላጅ የሆኑ ካድሬዎች ናቸዉ። ለምሳሌ ያክል ቆመስ አባ ወልደትንሳይ ቅድስት ማሪያምን፤ ቆመስ አባ መንግሰትአብ ቦሌ መድሀኔአለምን፤  አባ ወልደዳዊት ልደታ ቅድስት ማሪያምን፤ ቀሲስ ዘመንፈስቅዱስ ጎላ ሚካኤልን፤ቆመስ አባ እዝራ ወልደ ጊዮርጊስ የካ ቅዱስ ሚካኤልን፤ አባ ጥዑመ ልሳን ኪዳነ ማሪያም ገነተ ልዑል ቅዱስ ጊዮርጊስን፣ አባ  ተጠምቀ መድህን ገብረ ኢየሱስ ቅዱስ ራጉኤልን፤ አባ ኪሮስ ፀጋይ መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤልን እንዲሁም ቆመስ አባ ዕዝራ ገብረ ጊዮርጊስ ደግሞ ወልደ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ ቤተክርስያንን በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ። እነኚህና ሌሎችም ብዛት ያላቸዉ የትግራይ ክልል ተወላጅ የሆኑ አባቶች አብያተክርቲያናቱን የማስተዳደር ሹመት የተሰጣቸዉ ሆን ተብሎ የሌሎች ክልል አባቶችን በማስነሳት ሲሆን ዋና ስራቸዉም መንፈሳዊ ሳይሆን ህዝብን የማጋጨት አለማዊ ስራ እንደሆነ ከሰሯቸዉና አሁንም እየሰሩ ካሉት ስራ ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በንዲህ እያለ በስደት ላይ የሚገኘው ሲኖዶስ አዲስ የሚሾሙትን ፓትሪያርክ ህዝቡ እንዳይቀበል ጥሪ ማቅረቡን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በትናንትናው እለት ዘገበ። ሲኖዶሱ የላከለትን መግለጫ ዋቢ በማድረግ ኢሳት እንደገለጸው አገሪቱን እስር ቤት አድርጎ ህዝቡን በባርነት ለመግዛት የተነሳው ሀይል የቤተ ክርስቲያንን ሀዋርያዊና የነጻነት አንደበት ለመዘጋት ከሚጠቀምባቸው መንገዶች ተቀዳሚውና ዋነኛው ለህገ ቤተክርስቲያን ሳይሆን ለራሱ ፈቃድ ተገዢ የሆነ ሰው በፓትሪያርክ ስም በቤተ ክርስቲያን መንበር ላይ በማስቀመጥ ቤተክርስቲያንን መድፈር ነው ብሎአል።

ሲኖዶሱ "ላለፉት 21 አመታት በወያኔ አገዛዝ አስተባባሪነትና ደጋፊነት በህገ ወጥ መንገድ በተቀመጡት አባት ምክንያት ቤተ ክርስቲአንን ክፉኛ የጎዳው መከፋፈል እና መለያየት ሳያንስ አሁን ደግሞ እነዚህ ጥቂት ጳጳሳት በስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ መከታ አድርገው ፓትሪያርክ ብለው የሚሰይሙትም ፣ አባትነቱ የሀሰት አባት፣ ሹመቱም የሲሞን መሰርኢ ስለሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ አጥብቆ ያወግዘዋል። በተለይም ለቤተክርስቲያን ሰላምና አንድነት ከፍተኛ መስዋትነት በመክፈል የቆሙ እውነተኛዎቹ አባቶች በዚህ ሂደት ውስጥ ተሳታፊዎች ሆነው በታሪክም በእግዚአብሄርም ተወቃሾች እንዳይሆኑ" ጥሪ አቅርቧል። በመጨረሻም ሲኖዶሱ የቤተክርስቲያን ልጆች በአንድነት የሚቆሙበት ጊዜ አሁን መሆኑም በአጽንኦት ገልጿል።

## በአዲስ አበባ የቤት አፍርስ ዘመቻ ተጀመረ፤ የዘመቻው . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ህግና ስርአት በሌለባት ኢትዮጵያ ዜጎች የሚኖሩበትን አካባቢ እንዲፈናቀሉ የሚገደዱ ሲሆን ራሱ ወያኔ አለኝ በሚለው ህገ መንግስት ተብየ እንኩአን ባለንብረቶች ካሳ ሊከፋላቸዉና ቢያንስ ሦስት ወር ቤት የመፈለፍያ ግዜ ሊሰጣቸዉ ሲገባ  የኩማ ደመቅሳ አስተዳደር ግን  ከባቡር መስመር ዝርጋታ ጋር በተያያዘ በ22 አካባቢ ዜጎች ያለምንም ማስጠንቀቂያና ከሳ ክፍያ በአምስት ቀናት ጊዜያት ውስጥ ንብረታቸውን እንዲያነሱ ዜጎች በማስገደድ ላይ መሆኑን ዘጋቢያችን ገልጹአል።

የግንቦት ሰባት ዘጋቢያችንን ያናገሩ አንድ የቂርቆስ ነዋሪ እንደተናገሩት የግፈኛው ወያኔ አገዛዝ ጉዳይ አስፈጻሚ የሆነው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያለምንም ር ህራሄ ከመኖሪያ ቤታቸዉ ከአምስት ልጆቻቸው ጋር በግድ እንዳስወጣቸዉና ሜዳ ላይም እንደበተናቸው ተናግረዉ ህግ ተብየው በሚፈቅደው መሰረት ካሳ እንዲከፈላቸዉ ቢጠይቁም ግልምጫና ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው ተናግረዋል።

አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ አደራ ያሉን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግ ምሁር ለግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ በሰጡት ቃለ ምልልስ ደግሞ ወያኔ ህግ ማዉጣት ነዉ እንጂ ህግ ማክበር አያዉቅም። የኢትዮጵያ ህዝብ ግራ የገባዉ ነገር ቢኖር በማይከሰስና በማንም በማይዳኝ "ማን አለብኝ" አገዛዝ መገዛቱ ነዉ ብለዋል። የወያኔ አገዛዝ የዜጎችን ቤት ሲያሰኘዉ እያፈረሰ ፤እየወረሰ ወይም ከቤቱ ጋር በፍጹም የማይመጥን ካሳ እየከፈለ ዜጎችን ከቤታቸዉ እያስወጣ በየሜዳዉ ሲበትንና ህገ ምግቱን ሲጥስ የማይከሰስና የማይጠየቅ ከሆነ ወያኔ እራሱ ለምን ስለ ህገ መንግስት እንደሚያወራ አይገባኝም ብለዋል።

በኡራኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ የኮንስትራክሽን የፋብሪካ ውጤቶችን በማከፋፈልና በመቸርቸር የንግድ ስራ የተሰማሩና ወደአንድ ሺ የሚጠጉ ጊዜያዊና ቋሚ ሰራተኞች ያሏቸው ነጋዴዎችም በተመሳሳይ መልክ በአምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ እንዲለቁ መገደዳቸውን ጠቅሰው በሕግና በስርዓቱ ቢሆን ቢያንስ የ90 ቀናት ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው ይገባ እንደነበር ተናግረዋል፡፡ ምሁሩ ንግግራቸዉን በመቀጠል  የከንቲባነት ዘመኑ ሊጠናቀቅ ጥቅት ወራት ብቻ የቀረዉ ኩማ ደመቅሳ ካለመኖረያ ቤት ያስቀረዉ ህዘብ ብዛት ብዙ ህዝብ ባፈናቀልክ ቁጥር ትሸለማለህ የሉት ይመስላል ብለዋል።

# ሞት ለአስራሀንደኛው ቃል!!

ታሪኩ አባዳማ የካቲት 2005

**Those who can make you believe absurdities can make you commit atrocities** - Voltaire

መገናኛ ቴክኖሎጂ ባለፉት አስራአምስት ዓመታት ያስመዘገበው እመርታ ማንኛውም ሰው ያለ ብዙ ውጣ ውረድ ቤቱ ተቀምጦ ሀሳቡን ለማካፈል ዕድል እንዲያገኝ አስችሎታል። የመገናኛ አውታሮች ባለቤት ለመሆን የነበረው ጥያቄም በሚያስደንቅ ደረጃ ቀንሷል። ድረ-ገፅ ከፍቶ መጣጥፎች እና ወቅታዊ ዘገባዎችን ማስተናገድ እና ማሰራጪት በድምፅ እና ምስል ጭምር አጅቦ ዘገባ ማቅረብ ቀላል ነገር ሆኗል።

እርግጥ ነው ኮምፒዩተር ሸምቶ ፣ ኢንተርኔት ተከራይቶ በየድረ-ገፁ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ለመከታተል የገንዘብ አቅም ይጠይቃል። እኛ አገር የሰፈነው ሁዋላ ቀር አሰራር ወሀኒ የሚሰደው ወያኔአዊ ቁጥጥር ታክሎበት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ሊያደርገው ባይበቃም በውጭ ነዋሪ የሆነው ዜጋ ግን በዚህ የቴክኖሎጂ ትሩፋት በሰፊው እንደሚገለገል እናውቃለን።

ይህን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ጥልቀት ያላቸው ወቅታዊ ሀሳቦች በተከታታይ በማቅረብ ወገናቸውን ለማንቃት እና ለማነቃቃት ሚተጉ ምሁራን እያየን ነው። ሀሳባቸው አገር ቤት ደርሶ ቁሳዊ ሀይል ለመፍጠር ባይበቃም ተስፋ ሳይቆርጡ ድርሻቸውን ለማበርከት ምሁራኑ ሀሳብ ማካፈላቸውን በትጋት መቀጠላቸው ሊደነቅ ይገባዋል። ሁሉም ወገን በአንድ ሀሳብ ይዞታ ስር ስምምነት ደርሶ በአንድ ረድፍ ይሰለፋል ብሎ የሚጠብቅ ባይኖርም ቢያንስ የሰከነ ሀሳብ በመሰንዘር የውይይት ባህል ለማስፈን በመሞከራቸው ሊደነቁ የሚገባቸው ብዙ ምሁራን አሉን። ከዚህም ሌላ ድረ-ገፅ ከፍተው ሀሳቦች በነፃ እንዲንሸራሸሩ በማድረግ የጠየቀውን ግዜ እና አቅም ለዚህ በጎ ተግባር እያዋሉ የሚገኙ ወገኖቻችንም አድናቆት ሊቸራቸው ይገባል።

በቅንነት የሚሰነዘሩ አስተያየቶች እንዳሉ ሁሉ በተቀናበበረ ፖለቲካ ሸፍጥ ውዥንብር እና ማደናገር ለማስፈን የሚሰራጩ ዝባዝንኬዎች መኖራቸውን ሳንዘነጋ ከአገር ውስጥም ሆነ ውጭ በየዕለቱ ድረ-ገፅ ላይ የሚወጡ የግል አስተያየቶች ለውይይት ባህል መጎልበት ድርሻ እንዳላቸው ይገመታል።

በሌላ ወገን ደግሞ በቀላል ወጭ የኮምፒውተር ባለቤት ለመሆን የበቃው ዲያስፖራ ሀሳቡን በፅሁፍ ፣ በፓልቶክ ጎጆ ፣ በፌስቡክ… ይለዋወጣል ፣ አስተያየት ያቀርባል ፤ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ እንግዳ ጋብዞ ያስተናግዳል ፣ ይጠይቃል ፤ የሚስማማውን ይደግፋል - ያበረታታል ፣ የማይበጀውን ይረግማል… አንዳንዴም ያስፈራራል፡ ይደነፋል…። ድጋፉ ፣ እርግማኑ እና ድንፋታው ከፊሉ በድርጅት ፍቅር ሌላውም ከአገር ፍቅር ስሜት የመነጨ ቢመስልም በመካከሉ ገላጋይ ስለሌለ እንደ ጳጉሜ ካፊያ መቋጠሪያ አጥቶ ይነዛነዛል… ይጧጧታል። ቢያበረዩት ነዶ አያገኙበት ሙግት!!

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን - ጥሬም ሆነ ብስል ሀሳብን በነፃ መግለፅ የሚቻልበት መስኮት መኖሩ እንደ በጎ አጋጣሚ ሊታይ የሚገባው ነገር ነው። 'ተንፍስ' አለ ሀኪም… ማ ታፍኖ ይሞታል!!

አንዳንዴማ ዋልታ እና ማገር ፣ መያዣ መጨበጫ የሌለው ንትርክ መብዛቱ። መግቢያ እና መደምደሚያ የሌለው ዝባዝንኬ መበርከቱ… የመገናኛ አውታሩ እየሰፋ እና እየረቀቀ በሄደ መጠን ንትርኩ እየተለጠጠ - አንዱ ስለ ሰርግ ኬክ ሲያወራ ተቀባዩ ስለ ተዝካር ዘኬ - አንዱ ህብረት አንድነት ብሎ ሲማፀን ተቀባዩ አካኪ ዘራፍ አንቀፅ 39 እያለ እሳት ሲተፋ እንሰማለን…

ድረ-ገፅ ከፍተው ወይንም ፓልቶክ ጎጆ ቀልሰው አትድረሱብን የሚሉ 'የነፃ ሀሳብ' ተቆርቋሪዎችም እያጋጠሙን ነው። የግዛት ክልሉ እንተደፈረበት አርበኛ በደም ፍላት ስሜ ምን ሲደረግ ተነሳ ብለው የሚወራጩም ጥቂት አይደሉም - 'ኩት አትበሉን' ባዮችንም እየታዘብን ነው… በመላ የጠረጠሩትን ሁሉ በአፀፋ ለመስደብ የማይመለሱ ፣ በቀረበ ትችት ፍሬ ነገር ላይ ሳይሆን ግለሰብ ላይ ማነጣጠር ፣ መልዕክቱን ትተው መልዕክተኛውን መወረፍ የሚቀናቸው ፀሀይ የሞቁ 'ጋዜጠኞች' እየተቀላቀሉን ነው።

ይህም ሆኖ ፣ ብስል ይሁን ጥሬ በነፃነት የሚሰነዘሩ ሀሳቦች እየሰማን ነው።

በመረጡት ጎጆ መሳተፍ የሚቻል ቢሆንም በቀይ ካርድ መታቀብ ወይንም መታገድ መኖሩን ሁሉም ያውቃል። ይሁንና እዚህ በቀይ የወረደ በሌላ ጎጆ ዕጌረዳ ፍራሽ አንጥፎ የሚቀበለው በመኖሩ ሀሳቡ ተዳፍኖ አይቀርም። እዚህ መስማት የማይፈልጉት ነገር በሌላ መስኮት አደባባይ መውጣት መሰማቱ እንዳይቀር ቴክኖሎጂ የትናንሽ ምስለኔዎችን ስልጣን ለመስበር ታላቅ መሳሪያ ሆኗል - ይህም ሌላ በጎ ነገር ነው።

አገር ቤት በየመንደሩ የሚታየው ወገብ ይዞ አንገት እየሰበቁ መነታረክ እና አምበንሮ የመግጥም ባህል ወደ አለም አቀፋዊ መገናኛ መድረክ ተሸጋግሮ በየአህጉሩ ከኮምቲውተር ጀርባ በመሽጉ ድንበር ዘለል ሞጥሚጦች መካከል ሰጥ አገባው ቀጥሏል - ወፍም እንደ አገሩ እየጮኸ ነው!! ታይም… ውረድ…

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሞት ለአስራሀንደኛው ቃል!! . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

ይህንንም ያንንም በጎ ነው ማለቱ አለምክንያት አይደለም - ነፃነት በውበት አይለካም ፡ ነፃነት ጥራት ባለው አቀራረብ አይመዘንም ፤ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር አካባቢውን ፡ አስተዳደሩን ፡ አኗኗሩን ወይንም ከሌሎች ጋር ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት በሚመለከት አለኝ በሚለው ግንዛቤ መጠን በነፃነት ሀሳቡን መግለፅ ተፈጥሮ የለገሰው ፀጋ ነው። ነፃነት እራሱ ውበት ነው!!

ለእኛ ለፈረንጅ አገር ነዋሪዎች የፍልሰት (immigration) ህግ በኢኮኖሚ ረገድ ብቻ ሳይሆን የምዕራቡ አለም ቴክኖሎጂ ዕድገት ተጠቃሚ በመሆን እንደ ልብ ተገናኝተን ሀሳብ እንድንለዋወጥ ነፃ አውጥቶናል!!

ይሁንና የተሟላ ስብዕና ለመጎናፀፍ እምቅ ችሎታችንን ለተሻለ ህይወት እና አኗኗር መምጫ መሳሪያ ለማድረግ ፤ እንደ እንስሳ ሳይሆን እንደ ሰው ሀሳብ አመንጭተን ፡ ተለዋውጠን ፡ ተማምረን ተመራምረን እና ፈጠራ አዳብረን ለመገኘት የሀሳብ ልውውጡ ወግ እና ስርዓት ያለው ፡ በውጤት እና ትርፋማነት የሚለካ ሊሆን ይገባዋል። እንቶ ፈንቶ ሲፈተፍቱ ውለው ቢያድሩ የሚጨበጥ ነገር አይኖርም - እንዲሁ አፍ እንደተካፈቱ መኖር ደግሞ ከሰብአዊነት ደረጃ ዝቅ አድርገው በአፋኝ ህግጋት ፡ ሳንሱር እና ወከባ ስር እስካሁን ያቆየኑን አፋኝ ስርዓት አሜን ብሎ እንደመቀበል ያህል ያስቆጥራል።

እንደታዘብኩት ከሆነ ከአፍሪካ አገሮች የላቀ ፓልቶክ ጎጆ ተከፍቶ የምናገኘው (ሁሉም ዲያስፖራ ነው) በሱማልያውያን ሲሆን ኢትዮጵያውያን ደግሞ ሁለተኛውን ስፍራ ይዘው በንትርክ እየተንበሻበሹ ነው ፤ ኤርትራውያንም ከቅርብ ግዜ ወዲህ በርካታ ቁጥር ያለው ፓልቶክ ከፍተው ወግ እና ንትርኩን እያስነኩት ይገኛሉ። ከነኝህ ሶስት እጅግ ድሀ እና ሁዋላቀር ከሆኑ የምስራቅ አፍሪካ አገሮች የተሰደድን ዜጎች ላለፉት አስርት ዓመታት በየዕለቱ እየተገናኘን የ'ሀሳብ' ተኩስ ልውውጥ እናካሂዳለን። ገዢዎቻችን ያቆዩን እና ያተረፉልን ነገር ቢኖር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እየተባላን እና ሆዳችን እንደሻከረ አጎንብሶ መኖር ነው።

የሀሳብ ልውውጥ ለዕድገት ሳይሆን ለድቀት ለመራራቅ እና ለመደናቆር ሲዳርገን ቆም ብለን ራሳችንን ልንመረምር እና ሀሳብን - በነፃ ሀሳብ መልሰን መላልሰን ልንሞግተው ይገባል።

ከአፍሪካ በፓልቶክ ጎጆ ቁጥር ሱማልያ አንደኛ ፡ ኢትዮጵያ ሁለተኛ ፡ ኤርትራ ሶስተኛ… አራተኛ የለም።

ሌሎች አፍሪካውያን የሚወያዩበት ጉዳይ አጥተው ይሁን ወይም ከአገሩ ውጭ በስደት የሚኖረው ዜጋ ቁጥር አናሳ በመሆኑ መነሻው ምን እንደሆነ ባላውቅም የፖለቲካ ችግራቸውን በዚህ አይነቱ መድረክ ለመዳሰስ ፍላጎት እንዳላሳደሩ ማስተዋል ይቻላል። ሆኖም ጋናውያን እና ናይጄሪያውያን የሚጠቀሙባቸው አንዳንድ ጎጆ አላቸው - ጋና ናይጄሪያ ፓልቶክ ጎጆ የሚቀርቡት ግን ፖለቲካ ነክ ያልሆኑ ሀይማኖታዊ እና መዝናኛ ሙዚቃዎች ብቻ ናቸው። ይህ የሆነበት ምክንያት ሌሎች አፍሪካ አገሮች ሀሳብን በነፃነት ለመወያየት በዚያው በአገራቸው የተመቻቸላቸው ሌላ መድረክ በመኖሩ ይሆን? በጥሞና ሊጤን የሚገባው ነው።

እኛ ሀሳብን በነፃ የመግለፅ ጠኔ የፀናብን ነን ፡ የተራብን ነን - እነሱ ሀሳብን በነፃ መግለፅ ሞልቶ የተረፋቸው ቱጃሮች ናቸው። እኛ መስኮት ተገኘች ብለን ለመተንፈስ ስንራኮት እነሱ በተንጣለለው ፡ ወከክ ብሎ በተበረገደው በር ዘና ብለው ያውም በአገራቸው ፡ በቂያቸው ቁምነገር እየሰለቁ ናቸው - ሰሞኑን እንዳየነው በኬንያ ተፎካካሪ እጩ ፕሬዘደንቶች በቲቪ ቀጥታ የሚሰራጭ ክርክር እያደረጉ ነው። በሀሳብ ልውውጥ እና መረጃ ስርጭት ረገድ ምን ያህል ጥለውን እንደሄዱ ለመረዳት ጋዜጦቻቸውን አንብቡ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ 'አትግደል ፡ አታመንዝር…' ከሚለው አስርቱ ቃላት ግርጌ የተፃፈ አስራሀንደኛ ህግ አለ - 'በነፃ ሀሳብህን አትግለፅ' የሚል - እነ እስክንድር ነጋ ያንን አስራሀንደኛ ህግ ጥሰው ወህኒ ወርደዋል።

ስለሆነም በኛ ዜጎች መካከል እየታየ ያለውን መቋጫ ያጣ ንትርክ ሳስብ ከሁለት ዓመታት በፊት ለንባብ በቅቶ ፡ አምና ደግሞ በሲኒማ መልክ ተሰርቶ ብዙ አድናቆት የተቸረው The Hunger Games (የጠኔ ተኳሾች) በህሊናዬ ይመላለሳል። ፊልሙ በትክክል እንደሚያሳየው በጨካኝ ገዢዎች ቀንበር ስር ያሉ ህዝቦች እርስ በርስ እየተባሉ በጭካኔ እየተገዳደሉ እንዲቆዩ መገደዳቸው አዲስ ነገር እንዳልሆነ ያስገነዝባል።

እኛ የሙብት ረሀብተኞች እንጂ የሀሳብ ረሀብተኞች አለመሆናችንን ለሁሉም ወገን ማረጋገጥ የምንችለው በጋራ ሊያስተሳስረን በሚችል ሀሳብ ስር መታገል ስንበቃ - ግብ ላይ አተኩረን ስንታገል ብቻ ነው።

አስራሀንደኛውን የወያኔ ህግ ሲዋጉ ከተሰዉት ፡ ከተሰደዱትና ታፍነው ወህኒ ከሚማቅቁት አርበኞች ጎን እንሰለፍ!!


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው፡፡**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው፡፡



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን፡፡ g7radio@ginbot7.org